የሓ ቤተ ጥበብ
www.yehaarts.com
ያንብቡ . ይጻፉ . ይገናኙ፤ አሁን!
+251 (0) 912944937
+251 (0) 930015455
yehaarts@gmail.com
www.yehaarts.com




## አፈወርቅ ተክሌ›

‹“የእኔን ሥራ የሚያዩ ሁሉ ተስፋ እንዲያገኙ፣ ስለኢትዮጵያ እና ስለ አፍሪቃ ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸው፣ በፀሐይ ጮራ እንዲሞቁ፣ ከሁሉም በላይ ግን “ይቻላል” የሚል እምነት እንዲኖራቸው ፍላጎቴ ነው።” እጅግ የተከበሩ የዐለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ›

በ የሓ ቤተ ጥበብ || 2016-03-03
Read in PDF

### ፩) ትውልድ(ቀንና ቦታ)፣ ቤተሠብ፣ ትምህርት

በሰሜን ሸዋ በምትገኘው የሸዋ ነገሥታት ከተማ አንኮበር ላይ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ/ም ከአባታቸው አቶ ተክሌ ማሞ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ፈለቀች የማታወርቅ ተወለዱ። ሲሆን በስጋ የተለዩት ደግሞ ሚያዝያ ፪ ቀን ፳፻፬ ዓ/ም ነበር፡፡ ና በአሥራ አምስት ዓመታቸው በ ፲፱፻፵ ዓ/ም ለከፍተኛ ትምህርት ተመርጠው የምሕንድስና ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ እንግሊዝ አገር ተልከው በስመ ጥሩው የሎንዶን ዩኒቨርሲቲ የስሌድ ኪነ ጥበብ ማዕከል (Faculty of Fie Arts at Slade) የመጀመሪያው አፍሪቃዊ ተማሪ በመሆን ገብተው ተመረቁ።

ዞሮ ዞሮ ሞት አለና፤ የዓለም ሊቀ ሊቃውንት፣ እጅግ የተከበሩ ሰዓሊ አፈወርቅ ተክሌ ማክሰኞ፣ ሚያዝያ ፪ ቀን ፳፻፬ ዓ/ም በተወለዱ በ፸፱ ዓመታቸው፤ በቅርብ ባደረባቸው ጽኑ ሕመም በሕክምና እየተረዱ ሳለ በካዲስኮ ሆስፒታል አርፈዋል።

### ፪) ሙያ፣ አስተዋጽዖ፣ ተሰጥዖ

• አዲስ አበባ በ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ስዕሎች፣ ‘ሞዜይኮች’

• አዲስ አበባ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የሚገኘው የመጀመሪያው የ’ዳግመኛ ምጽዓት ፍርድ ስዕል

• በሐረር የልዑል ራስ መኮንን ሐውልት

• በአዲግራት የ’ዳግመኛ ምጽዓት ፍርድ ስዕል

• በሎንዶን ‘ታወር ኦፍ ለንደን’ የቅዱስ ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት ከብር እና ከእንጨት የተሠራ የመንበር መስቀል

• በሩሲያ፣ አሜሪካ እና በሴኔጋል ትርዒቶች የታዬው ‘የመስቀል አበባ’

• “እናት ኢትዮጵያ’

• የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ምስል

www.yehaarts.com

• ‘ደመራ’

• አዲስ አበባ በአፍሪቃ አዳራሽ መግቢያ የሚታየው በሎቶ ሃምሳ ካሬ ሜትር ላይ የተሳለው ትላቅ የመስታወት ስዕል፤ አንዱ የአፍሪቃን የቀድሞ ዕሮሮ፤ ሁለተኛው የአኅጉሯን የወቅቱን ትግል እና በሦስተኛው ደግሞ የዚችን ትላቅ አኅጉር የወደፊት ተስፋ የሚያሳዩ ናቸው

## ፫) መሰናክሎች፣ ማለፊያ ጥንካሬዎች

ፋንታሁን እንግዳ ‹ታሪካዊ መዝገበ-ሰብ› ባለው መጽሐፉ ‹‹…ትልቁ የኪነ ጥበብ ሰው ተሥፋዬ ገሠሠ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጀግና የሆኑትን አፈወርቅ ተክሌን ርዕሰ ጉዳይ አድርገው በልጅነታቸው በደረሰባቸው ‹ብልትን የመሰለብ› አደጋ ተሳልቀዋል፡፡ … ›› ብሏል፡፡ ይሄ አደጋ ከማሳለቅ ይብስ ያለ ትዳር ያለ ልጅ አስቀራቸው፡፡ በእርግጥ ወደ እድሚያቸው ማምሻ አንዲት ሴት አግብተው እንደነበርና ያልሰመረ ትዳር ሆኖባቸው ለሞታቸው አስተዋጽኦ እንዳለው ይነገራል፡፡

ሁለተኛውና የማይናቀው ፈተናቸው የማዕረጋቸው መርዘምና በሙሉ ስማቸው እንዲጠሩ መፈለጋቸው ነበር፡፡ ይህም ከብዙዎች ጋር እንዳራራቃቸው ይገመታል፡፡ ያም ቢሆን ስማቸው የልፋታቸው ዉጤት ነውና ከስሜ አንዲት እንኳ ጎድላ ብጠራ ‹አቤት አልልም› ማለታቸው ሙያቸውን ይበልጥ አስከብሮታል፡፡

## ፬) እሱን አጥተን ያጠነው ነገር

ዘመናዊ ስዕልን ወደ ኢትዮጵያ ካስተዋወቁት(ገብረ ክርስቶስ ደስታ እና እስክንድርም ተጠቃሾች ነበሩ) ዋነኛው ሰው ነበሩ፡፡ በልፋት የተገኘ ረዥም ስም ያላቸው ሰው ነበሩ፡፡ ለትምህርት የላከቻቸውን ሀገራቸውን ታምነው የተመለሱ ሰው ነበሩ፡፡ ኢትዮጵያን በያገሩ በጠና ያስተዋወቁ ብርቱ ሰው ነበሩ፡፡ እኛስ ያን ያህል እናውቃቸው፣ እናዘክራቸው፣ እንከተላቸዋለን ወይ?

## ፭) መርሆች፣ የህይወት ፍልስፍናው

ሊቁ ልበ ሙሉ ነበሩ፡፡ ኃይማኖተኛና ‹ዛሬ ከጨለሙብን ይልቅ ነገ የሚበራልን ይበልጣል› ባይ ተስፈኛም ነበሩ፡፡ ዋጋ ቢያስከፍላቸውም ራሳቸውን የሚያከብሩ ክቡር ሰው ነበሩ፡፡

## ፮) ምንጮቻችን

• ታሪካዊ መዝገበ ሰብ ቅጽ ሁለት፣ በፋንታሁን እንግዳ(ገጽ 187- 193)
• ኢቢኤስ የጥበብ ወሬዎች(እጅግ የተከበሩ የዐለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ)
•http://web.linkethiopia.org/guide-to-ethiopia/the-pankhurst-history-library/maitre-artist-afewerk-tekle/

www.yehaarts.com